# የእከክ በሽታን አስመልክቶ የግንዛቤ ማስጨበጫ





- የእከክ በሽታ በአይን በማይታይ የሰውን የቆዳ ክፍል ቦርቡራ በምትገባ ቅንቅን/ረቂቅ ተህዋስ/ አማካኝነት የሚመጣ ተላላፊ በሽታ ነው።

- የእከክ በሽታ በቀላሉ ተላላፊና በፍጥነት ከሰው ወደ ሰው በአካላዊ ንክኪ የሚዛመት የቆዳ በሽታ ነው።

- ማንኛውም ሰው በእከክ በሽታ የመያዝ እና የመጋለጥ ዕድል ቢኖረውም በተለየ ሁኔታ ተጠጋግተዉ የሚኖሩ፣ መኝታዎችን እና ልብሶችን የሚጋሩ የኅብረተሰብ ክፍሎች በይበልጥ ተጋላጭ ይሆናሉ። ለምሳሌ ፡- የአብነት ትምህርት ቤት ተማሪዎች ፣ ት/ቤቶች ፣ በእስር ቤት የሚገኙ ታራሚዎች ፣ በመጠለያ ቦታ ወይም ጊዜያዊ ማቆያ የሚገኙ ሰዎች ወ.ዘ.ተ.

- እናስተውል! የእከክ በሽታ መታከም የሚችል እና ጊዜያዊ የሆነ ህመም ነው። ስለዚህ የእከክ ታማሚዎች ተገቢውን ህክምና እና ክትትል በሚገባ ካደረጉ ከበሽታው በፍጥነት በመዳን ወደ ቀደመው መደበኛ ሕይወታቸው መመለስ ይችላሉ።

- የእከክ በሽታ በፍጥነት ሳይታከም ከተተወ ወደ ከፋ እና የተወሳሰበ ችግር ያመራል፤ ከፍተኛ የቆዳ ቁስለት እና ማሳከክ ያስከትላል።

**ተገቢውን ንጽህና መጠበቅ የእከክ በሽታ እንዳይዛመት ይረዳል**

- እርሶም ሆኑ ሌላ የሚያውቁት ሰው በእከክ በሽታ እንደተያዙ ካወቁ መላዉ ቤተሰብ በፍጥነት ወደ ህክምና ቦታ በመሄድ በሽታው በይበልጥ እንዳይስፋፋ ያድርጉ።

- ዋነኛው የእከክ በሽታ ህክምና በሐኪም ትእዛዝ የሚወሰዱ መድኃኒቶችን በሚገባ መውሰድ እና ንጽሕናን መጠበቅን ይጨምራል።

5S FOUNDATION

UKaid from the British people

FUNDED BY NIHR | National Institute for Health Research